# በጥንዶች ውስጥ የሚፈጸም ጥቃት ኣንቀበለውም !

**ሕጉ የቆመው ለማነው?**
ሕጉ የቤት-ውስጥ ጥቃት ሰለባ የሆነን ማንኛውንም ሰው ከጥቃት አድራጊው እና ከተጠቂው (የትዳር ጓደኛ ፣ የተመዘገቡ አጋሮች ፣ ቁባቶች ፣ ወዘተ) መካከል ያለው ግንኙነት ምንም ይሁን ምን ይከላከላል።

**የጥቃት ሰለባው የሆነው ግለሰብ ምን እርዳታ ሊቀበል ይችላል?**
ተጎጂው ሙሉ አድራሻቸውን ለላቪ(LAVI) ለተባለው ማእከል እንዲያስተላልፍ ፈቃደኛ ከሆነ ፣ ላቪ ማእከል ግለሰቡ ጋ ይደውላል (የኣስቸኳይ እርዳታ ካርዱን ይመልከቱ) ።
ተጎጂው በራሱ ተነሳሽነት የላቪ(LAVI) ማእከልን ማግኘት ይችላል። ነጻ ምክክርም እንዳለ ይነገረዋል።

ኣጥቂው ከተባረረ በኋላ ተጎጂው እቤት ውስጥ ለመቆየት ከፈለገ/ች ፣ ፖሊሶቹ የአደጋ ጊዜ እርዳታ ለማግኘት ወደ ኡሙስ (EMUS) እንዲደውል ይጠቁማል/ያሳስባል (የኣስቸኳይ እርዳታ ካርዱን ይመልከቱ)።

እንደዚሁም ተጎጂው የማሌፕሬሪ (MalleyPrairie) መቀበያ ማእከልን ማነጋገር ወይም ብድግ ብሎ ፣ ቀን ይሁን ሌሊት ወደዚያ መሄድ ይችላል (የኣስቸኳይ እርዳታ ካርድ ይመልከቱ)። የጥቃቱ ፈጻሚ ከቤት መባረር ተከትሎ ፣ በሁሉም የካንቶን ክልሎች የሚገኙት የማሌፕሬሪ ማእከሎችን ምክክር ያዘጋጃሉ ፣እቤት ድረስ በመምጣትም ምክክር ይሰጣሉ።

**ወንጀለኛው/ዋ ምን ዓይነት እርዳታ ሊቀበል/ልትቀበል ይችላል/ትችላለች?**
በፖሊስ ማስወጣት በሚከሰትበት ጊዜ ፣ ሰፕኣለ CPAle (የኣስቸኳይ እርዳታ ካርዱን ይመልከቱ) በስልክ ወይም በደብዳቤ የተባረረውን ሰው ጠርቶ ፣ ቢያንስ በአንድ የነፃ ግዴታ ማህበረሰባዊ እና ትምህርታዊ ቃለ መጠይቅ ያደርግለታል። ይኸውም የኣጥቂው ሁኔታ ለመመዘን እና በጥቃቱ በተሳተፉ ግለሰቦች ላይ የሚያስከትለውን መዘዝ ለማስታወቅ ያለመ ነው።

የተባረረው የጥቃት ፈጻሚ ግለሰብ ፣ ከኡሙስ (EMUS) እርዳታ ሊያገኝ ይችላል ፣ በተለይም በፍጥነት መጠለያ ማግኘትን በተመለከት ሊረዱት ይችላሉ።

የጥቃት ፈጻሚው ግለሰብ ፣ በራሱ/ራሷ ኣነሳሽነት ፣ የነጻ ምክር እና ኣቅጣጫ የሚያስይዝ ቃለ መጠይቅ ተጠቃሚ ለመሆን እንዲያስችለው CPALEን ማግኘት ይቻላል። CPALE ጥቃትን ለመቀነስ ስሜትን ለመቆጣጠር ያለመ ፕሮግራሞችን ይሰጣል።

**ሊባረር የሚችለው ማን ነው?**
ፖሊስ የቤት ውስጥ ጥቃት ፈጻሚውን ፣ ከጥንዶች የጋራ መኖሪያ-ቤት ወድያውኑ ማስወጣት ይችላል።

**መባረሩን የሚወስነው ማነው?**
ፖሊስ እንዳዲስ ተጨማሪ ጥቃት እንዳይደርስ በማሰብ ጥቃት ፈጻሚውን ያባርራል። ተጎጂው/ተጠቂው ይህንን እርምጃ መቃወም አይችልም። እርምጃው ስልታዊ በሆነ መንገድ ለፍርድ ቤት ይቀርብና እሱም ትዕዛዝ ውሳኔ በመወሰን በአስራ አራት ቀናት ውስጥ የችሎት ቀጠሮ ይሰጣል።

**የጥንዶቹ የጋራ ቤት ፣ ባለቤት ወይም ተከራይ መሆን ፣ከመኖሪያ ቤት የመባረሩን እርምጃ ላይ ተጽእኖ ኣለው ወይ?**
ኣይ አይደለም ፣ ይህ ምንም ዓይነት ሚና የለውም። የመኖሪያ ቤቱ ባለቤትም ሆነ ብቸኛ የኪራይ ውል ፈራሚ ፣ ፖሊስ ጥቃት የሚፈጽም ማንኛውንም ሰው ማባረር/ማስወጣት ይችላል።

**የተባረረው ሰው ምን መውሰድ ይችላል?**
ለግለሰቡ/ቧ አስፈላጊ የሆኑትን ግላዊ በጣም ኣስፈላጊ ቁሳቁሶች (ለምሳሌ የግል ሰነዶቹ/ቿን ፣ ልብሶቹ/ቿን ፣ መድሀኒቶቹ/ቿን ፣ የራሱ/ሷን ላፕቶፕ ፣ ወዘተ) መውሰድ ይችላል/ትችላለች።

**መባረሩ ለምን ያህል ጊዜ ነው?**
ከጥንዶቹ መኖርያ-ቤት መባረሩ ግዜ ቢበዛ ለሰላሳ ቀናት ነው።ኣስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ፣ ፍርድ ቤቱ ተጥይቆ ፣ እንደገና መባረርን ጨምሮ, ፣ ሌሎች እርምጃዎችን መውሰድ ይችላል።

**የተባረረው ግለሰብ ከተረጋጋ በኋላ መመለስ ይችላል ወይ?**
ኣይ አይደለም ፣ የተወሰነበት የመባረሩ የግዜ ገደብ ከማብቃቱ በፊት መመለስ ኣይችልም። መባረሩ ሁለቱም ወገኖች ሁኔታውን እንዲያስቡበት እና አስፈላጊ ከሆነ አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስዱ ያስችላቸዋል.

**የተባረረው ሰው ክልከላዎችን ካላከበረ ምን መደረግ ኣለበት?**
ተጎጂው ለተባረረው ሰው በሩን መክፈት የለበትም። በአስቸኳይ ፖሊስ ጋ በመደወል ፣ ከቤት መባረር አስቀድሞ መደረጉን መጥቀስ አለበት። አስፈላጊ ከሆነ ተጎጂው በፍርድ ቤት የወሰነውን የመልቀቂያ ትእዛዝ ለፖሊስ ያሳየዋል።

ከጥንዶቹ ቤት የተባረረውን ሰው ፣ ማራቅ ሃላፊነቱ የፖሊስ ነው ፣ ኣስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም በማስገደድ ያስወጣል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ክልከላውን ችላ ማለት የወንጀል ቅጣት ሊያስከትል ይችላል።

....

AMHARIQUE

# የኣስቸኳይ እርዳታ ካርድ

**ድንገተኛ አደጋ**

**ፖሊስ** | ለማንኛውም ድንገት ለ24 ሰኣታት ፣ ቀንና ሌሊት
117 ወይም 112

**የድንገተኛ ሕክምና** | ለ24 ሰኣታት ፣ ቀንና ሌሊት
144

**Équipe Mobile d'Urgences Sociales (EMUS)** | ለ24 ሰኣታት ፣ ቀንና ሌሊት ፣ ስልክ ቊ
0848 133 133

**ለተጎጂዎች እርዳታ**

**Centre d'accueil MalleyPrairie** | ለ24 ሰኣታት ፣ ቀንና ሌሊት ፣ ችግርዎትን ማዳመጥ እና መጠለያ ኣገልግሎት ይሰጣል
Chemin de la Prairie 34 – 1007 Lausanne
021 620 76 76 – info@malleyprairie.ch

**Centre LAVI** | ለተጎጂዎች እርዳታ
Rue du Grand-Pont 2 bis – 1003 Lausanne
021 631 03 00
–
Rue de la Plaine 2 – 1400 Yverdon-les-Bains
021 631 03 08
–
Rue du Molage 36 – 1860 Aigle
021 631 03 04

**ለጥቃት ፈጻሚዎች ምክር**

**Centre Prévention de l'Ale (CPAle)**
Rue de l'Ale 30 – 1003 Lausanne
021 321 24 00 – info@prevention-ale.ch

**የመኖሪያ ፍቃድ/ፐርሚ**

**La Fraternité du CSP** | ስለ የመኖሪያ ፈቃድ ጥያቄ የሚመለከት
Place M.-L. Arlaud 2 – 1003 Lausanne
021 560 60 98 – frat@csp-vd.ch

## የመኖሪያ ፍቃድ

**Service de la population** | የመኖሪያ ፈቃድ ባለስልጣን
Av. de Beaulieu 19 – 1014 Lausanne

## የሕክምና ሁኔታ ሪፖርት

**Unité de médecine des violences**
(የጥቃት ሰለባዎች መታከምያ ክፍል)

**CHUV**
Rue du Bugnon 44 – 1011 Lausanne
021 314 00 60

**Hôpital d'Yverdon-les-Bains**
Rue d'Entremonts 11 – 1400 Yverdon-les-Bains
024 424 42 20

**Hôpital Riviera-Chablais – Espace Santé Rennaz**
Route des Tilles 6A – 1847 Rennaz
058 773 64 77

**Hôpital de Nyon**
Chemin Monastier 10 – 1260 Nyon
021 314 08 51

## የአከባቢ ፍርድ ቤቶች

**Tribunal d'arrondissement de Lausanne**
Palais de justice de Montbenon
Allée E.-Ansermet 2 – 1014 Lausanne

**Tribunal d'arrondissement de la Broye et du Nord vaudois**
Rue des Moulins 8 – Case postale – 1401 Yverdon-les-Bains

**Tribunal d'arrondissement de l'Est vaudois**
Cour-au-Chantre – Rue du Simplon 22 – 1800 Vevey

**Tribunal d'arrondissement de La Côte**
Route de Saint-Cergue 38 – 1260 Nyon

**www.violencequefaire.ch**
ማንነታቸው ሳይገልጹ ጥያቄዎችዎን የሚጠይቁበት ዌብ ሳይት/ድር ጣቢያ

**Bureau de l'égalité**
(የሴቶች የወንዶች እኩልነት ቢሮ)
021 316 61 24 – info.befh@vd.ch
www.vd.ch/violence-domestique

...

የተባረረው ግለሰብ ኣንዳንድ ነገሮች (ልብሶች, ሰነዶች, ወዘተ) እንደሚያስፈልጋቸው ካመለከቱ ፣አብረዋቸው ወደ ቤታቸው እንዲሄዱ ፣ ፖሊሶችን ማነጋገር አለባቸው።

በስልክ መልእክት ማንኛውም ትንኮሳ ሲከሰት ተጎጂው/ተጠቂው ምላሽ መስጠት የለበትም። ፍርድ ቤቱን ኣጥቂው በምንም ዓይነት መንገድ እንዳያገኘው/ኛት እንዲከለክል እና የቴሌኮሙኒኬሽን ተከላ አላግባብ በመጠቀሟ የወንጀል ክስ መመስረት መጠየቅ ይችላል/ትችላለች።

**ስደተኛ የሆነ ሰው ፣ ከጥንዶቹ ቤት ከተባረረ የመኖሪያ ፈቃዱን/ፐርሚውን ያጣል ወይ?**
አይ ኣይደለም ፣ ከቤት ማስወጣቱ ከጥቃት ለመከላከል የአጭር ጊዜ ዘዴ ብቻ ነው። የተጎጂው የመኖሪያ ፈቃድ ከተባረረው ግለሰብ ጋር የተያያዘ ከሆነ ፣ ለረጅም ጊዜ መለያየት በሚፈጠርበት ጊዜ ከሲኤስፒ CSP (የኣስቸኳይ እርዳታ ካርዱንይመልከቱ) ጋር መጠየቅ/ማነጋገር ይመከራል።

## ለደህንነትዎ ይጠንቀቁ

ወንጀለኛውን ከሀገር የማስወጣት እድሉ ተጎጂው በቤት ውስጥ እንዲቆይ ያስችለዋል. ነገር ግን ፣ ለተጨማሪ ጥቃት ፍፁም ጥበቃ መስጠት ኣይችልም።

ጥቃትና እንግልት ካለበት ግንኙነት ለመላቀቅ ከባድ እና ጊዜ የሚወስድ ነው። በእንደዚህ ዓይነት ጊዜ ውስጥ ፣ ማንኛውንም ኣለ የተባለው እርዳታ መጠቀም በጣም አስፈላጊ ነው።

ኣደጋ ሲከሰት

**የፖሊሶች የኣደጋ እርዳታ መጥርያ ስልኮች**
**117 ወይም 112**

design CULLYCULLY.STUDIO - © 2022 - BEFH

canton de vaud

# የሚማታው ይባረራል !

በጥንዶች መካከል በቤት - ውስጥ ጥቃት ፈጻሚዎች መርጃና ምክር

Bureau de l'égalité entre les femmes et les hommes